# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 160 ሰኔ 2 2003 ገጽ 1

**"እኔ ከሌለሁ አገሪቷ ትበተናለች፤ ስለዚህም በጭራሽ ስልጣኔን አልለቅም" ያለው የየመኑ መሪ አሊ አብደላ ሳልህ በባሩድ ፊቱና ጀርባው ተለብልቦ ሳውዲ ዓረቢያ ውስጥ የአልጋ ቁራኛ ሆኗል። ለብዙዎች የአሊ አብደላ ሳልህ የስልጣን ዘመን አብቅቷል። ከቁስሉ አገግሞ ወደ የመን ቢመለስ እንኳን የምትጠብቀው እሱ የማያውቃት የመን ናት።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## መነሻ ዋጋው አምስት መቶ ብር የነበረው የአባይ ቦንድ ግዢ ወደ ሃምሳ ብር መ ውረዱና፣ ህዝቡ በበኩሉ ገንዘባችንን ለጦር መሳሪያ ግዢ አንሰጥም ማለቱ ተሰማ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከሁለት ወር በፊት አባይን ለመገደብ ማቀዱን ይፋ ባደረገበት ጊዜ በጉልበትና በማስፈራራት ታየ ተብሎ የነበረው የህዝብ ተነሳሽነት በአሁኑ ጊዜ መጥፋቱንና፣ ህዝቡ ገንዘባችንን ለጦር መሳሪያ መግዣ አናውልም ማለት መጀመሩን የኢትዮጵያ ሳተላይይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘጋቢዉን ዋቢ በማድረግ ዘገበ።

የህዝቡ ተነሳሽነት ከወር ባልበለጠ ጊዜ ክፉኛ በመሟሸሹ የተደናገጠው የሰው በላው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ቀደም ሲል ከያንዳንዱ ቤተሰብ ለመሰብሰባ አቅዶት የነበረውን 500 ብር የአንድ ቦንድ መግዣ ዋጋ በአስር እጥፍ በመቀነስ ወደ 50 ብር ዝቅ ለማድረግ መገደዱን ለማወቅ ተችሎአል።

አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የመንግስት ሰራተኛ ለኢሳት ዘጋቢ እንደገለጹት፤ አገራችን ለዘመናት በአባይ ወንዝ ላይ እንዳትጠቀም የወጪ ሃይሎች የሚሸርቡትን ሴራ ለማክሸፍ በሚመስል እርምጃ አባይን ልንገድብ ነው በማለት የህዝቡን የአገር ፍቅር ስሜት በመቆርቆር የትኩረት አቅጣጫ ለማሳት የተደረገው ጥረት ከሁለት ወር ባልበለጠ ጊዜ እርቃኑን (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ጋር ውይይት ያካሄዱት ኢትዮጵያዊያን አርቲስቶች ለዘረኛው አምባገነን ያበረከቱት የወርቅ ብእር ስጦታ እጅግ አሳፋሪ ነው ተባለ

ባለፈው ሰኞ በአዲስ አበባ ከተማ ከ1500 በላይ ኢትዮጵያዊያን አርቲስቶች ከዘረኛውና አምባገነኑ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ጋር ስብሰባ ያካሄዱ ሲሆን፣ በዚሁ እለት አርቲስቶቹ ያዘጋጁትን የወርቅ ብእር ስጦታ ማበርከታቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በአዲስ አበባ ከተማ የተካሄደው የአርቲስቶቹ ስብሰባ በግማሽ ቀን የተጠናቀቀ ሲሆን የስብሰባው ዋናና ብቸኛ የመወያያ ርእስ በቅጂ መብት ጉዳይ ዙሪያ በሃገሪቱ እየታየ ያለው ህጋዊ ያልሆነ ጥሰት ሊወገድ በሚችልበት ሁኔታ ላይ እንደነበር ታውቁአል።

የዚሁ ስብሰባ ሂደት በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር በሚገኙት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የተዘገበ ሲሆን የውጭ ሀገራት ሚዲያ ዘጋቢዎች በስብሰባው እንዲገኙ እድሉ እንዳልተሰጣቸው ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቶአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከወያኔ ታማኝ ሎሌዎች አንዱ የሆነው ተስፋየ ሃቢሶ በአእምሮ ፈጠራ ስርቆት ተግባር መሰማራቱ ተጋለጠ

ወያኔ ሥልጣን ከያዘበት ማግሥት ጀምሮ ከሽግግር መንግሥት ጸሃፊነት እስከ አምባሳደርነት ባሉት የተለያዩ የስልጣን እርከኖች በመሾም ሎሌነቱን በተግባር ያስመሰከረው ተስፋየ ሃቢሶ ዶክተር ኮሊን ዳርች የተባሉ በእንግሊዝ ሃገር የተወለዱ ደቡብ አፍሪቃዊ ምሁር በኢትዮጵያ ላይ ጥናት በማድረግ ያወጡትን የምርምር ውጤት ጽሁፍ አንድም ቃል ሳይቀይር እንዳለ የራሱ የምርምር ውጤት አድርጎ በኢህአደግ ድህረገጽ ላይ ማሳተሙን ጋዜጠኛ አበበ ገላው አጋለጠ።

ተስፋየ ሃቢሶ የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ኣጫፋሪና ደጋፊ በሆኑት እንደ አይጋ ፎረም፣ ኢትዮጵያ ፈርስት፣ እንዲሁም ትግራይ ኦን ላይን ላይ የተለያዩ ጽሁፎችን በማውጣት የሚታወቅ ሲሆን፣ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በ 2002 በተደረገው ምርጫ 99.6 በመቶ በሆነ ድምጽ ህዝብ መርጦኛል ብሎ ሲያውጅ የምርጫ ውጤቱ ትክክል አለመሆኑን የውጭ ታዛቢዎች እየመሰከሩ ባለበት ሁኔታ ምርጫው ትክክለኛና ፍትሃዊ ነበር በማለት ሲጽፍ እንደነበር ይታወሳል።

ተስፋዬ ሃቢሶ በስርቆት የራሱ አስመስሎ ያወጣው የጽሁፉ ርእስ በእንግሊዝኛ አጠራሩ "The Ethiopian Student Movement in the Struggle against Imperialism, 1960-1974." እንደሆነ የገለጸው ጋዜጠኛ አበበ ገላው፣ ይህን የምርምር ውጤት የሰሩትን ዶር ኮሊን ዳርች በኢሜይል ስለተፈጸመው የአእምሮ ውጤት ዘረፋ የገለጸላቸው ሲሆን ምሁሩ በተፈጸመው ድርጊት እጂግ መገረማቸው ታውቁአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በዙሪያው ያሰባሰባቸው ባለስልጣናት ሁሉ በራሳቸው የማይተማመኑና ስብዕናቸውን ለጊዚያዊ ጥቅም የሸጡ በመሆናቸው ከአገር ሃብት ዘረፋ እስከ የአዕምሮ ውጤት ዘረፋ መሰማራታቸው ቀድሞውኑ ከህዝብ የተሰወረ አይደለም ያሉን አንድ የዩኒቨርሲቲ መምህር ወያኔ ስልጣን በያዘበት ወቅት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ስለማጠናቀቃቸው ማስረጃ ያልነበራቸው ሁሉ ሌሎች እየተፈተኑላቸው ከተልዕኮ ትምህርት ቤቶች የተሸመቱ ዲግሪዎች ባለቤት መሆናቸው ጸሃይ የሞቀው ምስጥር ነው ብለዋል።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የግንቦት ሃያ በአልን ያከበረው በከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ ተውጦ እንደነበር አመነ

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ባለፈው ሳምንት ሃያኛውን የንግሥና አመት በአሉን ለማክበር በሚሊኒዬም አዳራሽ ለተሰበሰበት ደጋፊዎቹ ባደረገው የመዝጊያ ንግግር ፣ "የመስቀል አደባባይን የጣህሪር አደባባይ እናደርጋለን "በማለት ያሰቡ ሃይሎች ሃሳባቸው ሳይሳካ መቅረቱ ከፍተኛ ድል ነው ማለቱን የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ ገለጸ፣ እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ዘረኛው መለስ ባደረገው ንግግር የመጀመሪያ ክፍል የግንቦት ሃያ በአል ከመቼውም በላይ ደምቆ የተከበረበት ምክንያት የመስቀል አደባባይን የጣህሪር አደባባይ እናደርጋለን ብለው ከዛቱ ነውጠኞች ጋር እልህ በመጋባት አይደለም በማለት "ነውጠኞች" ያላቸው ሃይሎች ምን ያህል የመንፈስ መረበሽ ፈጥረውበት እንደነበረ የሚያመላክት ንግግር አድርጎአል። በፊቱ ላይ ምንም አይነት ፈገግታ ሳይታይበትና በየመሃሉም የጉሮሮ መድረቅ እያሳለው ለአድናቂዎቹና ለእንጀራ ሲሉ ጥሪውን አክብረው በአዳራሹ ለተገኙት ሆዳሞች ባደረገው በዚህ ንግግር በአሉን ለማድመቅ በመስቀል አደባባይ የተገኘውን ህዝብ ከልብ እንደሚያመሰግን ገልጾ ፤የበአሉ አከባበር የፈጀው ጊዜ ከወትሮው በተለየ አጭር እንደነበርና በዚህም ምክንያት ከቤታቸው ወጥተው የሰልፉ አደባባይ ሳይደርሱ ስብሰባው በመጠናቀቁ ከመንገድ የተመለሱ ሁሉ መስቀል አደባባይ ከተገኘው ህዝብ በበለጠ ምስጋና ይገባቸዋል በማለት የምጸት ንግግር መናገሩን የደረሰን ዘገባ ያስረዳል። ከግንቦት ሃያ በአል ጋር በተያያዘ ለዘረኛው አገዛዝ ቅርበት እንዳለው የሚታወቀው የሪፖርተር ጋዜጣ ባወጣው ዘገባ ግንቦት 20 ቀን 2003 ዓ.ም. በተካሄደው የድጋፍ ሰላማዊ ሠልፍ ያልተገኙ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ሠራተኞች በሰልፉ ላይ ያልተገኙበትን ምክንያት የሚያስረዳ ማስረጃ በሦስት ቀን ውስጥ እንዲያቀርቡ መታዘዙን ገልጾአል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የሰው ኃይል አስተዳደር ደጋፊ የሥራ ሒደት መሪ ስምና ፊርማ አርፎበት ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም. በመሥሪያ ቤቱ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በተለጠፈው ማስታወቂያ ላይ፣ ግንቦት 20 ቀን በተደረገው አገር አቀፍ ጥሪ ያልተገኙ ሠራተኞች ያልተገኙበትን ምክንያት የሚገልጽ ማስረጃ በሦስት ቀን ውስጥ ማቅረብ እንዳለባቸው መገለጹን አስታውቁአል፡፡ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ጥራትና ደረጃውን ያልጠበቀ ዘይት ለህዝብ እየተሸጠ ነው፣ የዘረኛው አገዛዝ የሚመለከተው ባለስልጣን እንዲህ አይነት ዘይት ሁለተኛ ወደ ሃገር ውስጥ አይገባም አለ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መጥቶ ባለፉት ጥቂት ወራት ብቻ መሰረታዊ የምግብ እቃዎች ከገበያ ጭራሹኑ እስኪጠፉ ድረስ መድረሱ፣ ይህንም ተከትሎ በተለይም በምግብ ዘይት ለተፈጠረው እጥረት የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ኢትዮጵያ ውስጥ የዘይት ሃይቅ ፈጥረን ሃገሪቱን በዘይት እናጥለቀልቃታለን ማለቱ የሚታወስ ሲሆን ይህን ንግግሩን ተከትሎ ጥራትና ደረጃውን ያልጠበቀ ዘይት በብዛት ወደ ሃገር ውስጥ ገብቶ ሽያጭ ላይ መዋሉን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ አመለከተ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በድህነት አረንቋአ ተዘፍቀው የሚገኙት እጂግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ምንም አይነት ሌላ አማራጭ ባለማግኘታቸው ይህን የምግብ ዘይት ገዝተው በመጠቀም ላይ ናቸው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ወቅታዊውን የምግብ ዘይት እጥረት ለመፍታት ዘረኛው አገዛዝ በሸማቾች ማኅበር አማካይነት ቀደም ሲል ለኅብረተሰቡ እንዲያዳረስ ያከፋፈላቸውና መረጃቸው ሙሉ በሙሉ በዓረብኛ የሆነ ዘይቶች፣ ከእንግዲህ ወደ አገሪቱ እንደማይገቡ የአገዛዙ የተስማሚነትና ምዘና ድርጅት ማስታወቁን፡ በዓለም አቀፍ የጥራትና ደረጃዎች ሕግ መሠረት የተሠራጨው ዘይት የእንግሊዝኛ ወይም የአማርኛ መግለጫ እንዲኖረው እንደሚያስገድድ፡ ነገር ግን የተከፋፈለው ዘይት ላይ ያለው መግለጫ ሙሉ በሙሉ ዓረብኛ በመሆኑ፣ የተመረተበትንና አገልግሎቱ የሚያበቃበትን እንዲሁም ከምን እንደተመረተ ማወቅ ተጠቃሚውን ግራ ማጋባቱ ይታወሳል ሲል ለአገዛዙ ቅርበት ያለው ሪፖርት ጋዜጣ ዘገበ፡፡(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን እስረኞችን ማሰቃየቱን እንደቀጠለ መሆኑ ተዘገበ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወይኔ አገዛዝ በሕገወጥነት ካሰራቸው የኦሮሞ ፌዴራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን) ፓርቲ 300 በላይ አባላቶች እና ደጋፊዎች መካከል 240ዎቹ እስከ አሁን ፖሊስ ምርመራዬን አልጨረስኩም በማለቱ በቤተሰቦቻቸው፣ በጠበቆቻቸው እና በፓርቲያቸው እንዲጎበኙ አለመፈቀዱን ፡ እስረኞቹ በአሁኑ ወቅት በምን ሁኔታ እንደሚገኙ እንደማይታወቅ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

እንደ ኢሳት ዘገባ ከአራት ወራት በፊት በማዕከላዊ ምርመራ ቢሮ የታሰሩት 60 የኦፌዴን አባላቶች ብቻ በቅርቡ ወደ ቃሊቲ ማረሚያ ቤት መዘዋወራቸውንና፣ ፍርድ ቤት ለሰኔ 22 ቀን 2003 ዓ.ም ቀነ ቀጠሮ የሰጠባቸው በመሆኑ ሰሞኑን በቤተሰቦቻቸው የመጎብኘት ዕድል ማግኘታቸው ታውቁአል።

የኦፌዴን ፓርቲ ዋና ጸሐፊ አቶ በቀለ ነጋን በመጥቀስ ኢሳት ባወጣው ዘገባው "የኦፌዴን አባላቶችና ደጋፊዎችን የማሰሩ ተግባር አልቆመም ፣ በኢሊባቡር በበደሌ ዞን፣ በምዕራብ ሸዋ ባኮ አካባቢ፣ እንዲሁም በጉጂ ዞን እና (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

# ከየመን ህዝባዊ አብዮት ምን እንማራለን?

ህዝባዊ አብዮት ከተቀጣጠለባቸው የአረብ አገራት ሁሉ በመልክዓ ምድር አቀማመጥ የየመንን ያህል የሚቀርበን የለም። የኢትዮጵያና የየመን መመሳሰል በመልክዓ ምድር አቀማመጥ ብቻ አይደለም፤ መመሳሰላችን በብዙ ጉዳዮች ነው።

1. የመን የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የነገሰባት አገር ናት፤ ወይም ነበረች። አሊ አብደላ ሳልህ ለሰላሳ ሶስት ዓመታት ገዝቷታል። ኢትዮጵያም የአንድ ሰው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የነገሰባት አገር ናት። መለስ ዜናዊ ለሃያ ዓመታት ገዝቷታል።
2. የመን በበርካታ ዘውጌ ማኅበረሰቦች (ብሄር፣ ብሄረሰቦች) የተገነባች አገር ስትሆን አሊ አደብላ ሳልህ በተግባር የየመንን ህዝብ እርስ በርሱ እያጋጨና እያስታረቀ ሲገዛ፤ በወሬ ደግሞ ተበታትና የነበረችውን የመን አገናኝቶና አዋድዶ ያቆያት አስመልሎ ሲሰብክ ኖሯል። የኛው ጉድም ኢትዮጵያን ከመበታተን ያዳንናት እኔና ጓደኞቼ ነን ማለቱ ሳያንሰው ለወደፊቱም እኛ ከሌለንም  መበታተኗ አይቀሬ ነው እያለ ያስፈራራል።
3. የመን ከአረብ አገሮች ሁሉ በድህነት የመጨረሻው ደረጃ ላይ ያለች አገር ናት። ኢትዮጵያም በድህነት ከአፍሪቃ - በዚህም ምክንያት ከዓለም - አገሮች የመጨረሻ ደረጃ ላይ ያለች ናት።የአሊ አብደላ ሳልህ አገዛዝ "ስለፈጣን እድገት" ሲናገር የቆየ ቢሆንም የመን ዜጎቿ በመሃይነትና በበሽታዎች የተጎዱባት እና ኋላ ቀር ባህል የሰፈነባት አገር ናት። የኛዋ ኢትዮጵያዋም የፈጣን እድገት መዝሙር የሚዘመርባት ቢሆንም ዜጎቿ ከየመን በባሰ ሁኔታ በመሃይምነትና በበሽታ እየማቀቁ ያሉባት አገር ናት።
4. "የመን የአሊ አብድላ ሳሊህ የከሰረ የቤተሰብ ቢዝነስ ነች፤ መንግስቷም ከወደቁ መንግሥታት ተርታ ነው" ተብሏል። ኢትዮጵያም የመለስ ዜናዊና ቡድኑ የግል ሃብት ሆናለች። በመለስ እጅ ያለችው ኢትዮጵያዊ እየተመዘበረች፤ ለአረቦችና ህንዶች እየተሸጠች ከስራለች፤ እየከሰረችም ነው። መለስ የሚጫወትባት ኢትዮጵያችንም ከወደቁ መንግሥታት ተርታ ገብታለች።
5. የመን ውስጥ የኢንተርኔት ተጠቃሚው እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ በዘመናዊ የመገኛና ዘዴዎች ለአመጽ መጠራራት የማይሞከር እንደሆነ ሲነገር ነበር። በዚህም ምክንያት የአሊ አብደላ ሳልህ ካድሬዎች ብቻ ሳይሆኑ ገለልተኛ የሆኑ ምሁራንም ሳይቀሩ የቱኒዚያና የግብጹ አይነቱ አብዮት የመን ውስጥ የማይሞከር ነው ሲሉ ነበር። ኢትዮጵያም ውስጥ የኢንተርኔት ተጠቃሚው ቁጥር እጅግ አነስተኛ በመሆኑ ተመሳሳይ ህዝባዊ አብዮት የመቀስቀሱ እድል አሳንሰው የሚያዩ በርካቶች ናቸው።
6. አሊ አብደላ ሳልህ ራሱን የፀረ-ሽብርተኝነት ትግል አጋር አድርጎ በማቅረብ የአሜሪካና የአውሮፓ መንግሥታትን ድጋፍ በሰፊው ሲያገኝ ቆይቷል። የኛው መለስም የአካባቢው ፀረ-ሽብርተኝነት ትግል አጋር ሆኖ በመቅረብ እያጭበረበረ ነው።
7. ኣሊ ኣብደላ ሳልህ በሰላዮቹና አልሞ ተኳሽ ወታደሮቹ ብዛት ህዝብን በማስፈራራቱ አንዳችም የተቃውሞ እንቅስቃሴ የማይታሰብ መሆኑ ሲወራ ነበር። የኛው መለስም ጆሮጠቢዎችና አጋዚዎችን በብዛት በማሰማራቱ፤ ህዝብም እርስ በርሱ እንዳይተማመን በማድረጉ አብዮት የማይታሰብ ነው የሚሉ አልጠፉም።
8. የመናዊያን "ጫት አፋቸውን ስለሞላው የተቃውሞ ጩኸት ማሰማት አይችሉም" ተብሎ ተቀልዶባቸው ነበር። በኢትዮጵያ ህዝብና ወጣት የትግል ሞራል ላይ የሚሳለቁም ብዙዎች ናቸው።

በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ባለችው የመን ውስጥ ህዝባዊ አብዮት ተቀሰቀሰ። የመናዊያን እንደ ቱኒዚያና ግብጽ የዓለም ዓቀፍ መገናኛ ብዙሃን ትኩረት አልሳቡም። አልጀዚራም ቢሆን የየመንን አብዮት እንደግብጽ በተከታታይ አልዘገበም። ይህ ሁሉ ግን የመናዊያንን ተስፋ አላስቆረጠም።

የመናዊያን ከአራት ወራት በላይ የአሊ አብደላ ሳልህን አገዛዝ ተጋፈጡት። በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የህይወትና የአካል መስዋዕትነት ከፍለው እነሆ ዛሬ ለድል ተቃርበዋል።

"እኔ ከሌለሁ አገሪቷ ትበተናለች፤ ስለዚህም በጭራሽ ስልጣኔን አልለቅም" ያለው አሊ አብደላ ሳልህ በባሩድ ፊቱና ጀርባው ተለብልቦ ሳውዲ ዓረቢያ ውስጥ የአልጋ ቁራኛ ሆኗል። ለብዙዎች የአሊ አብደላ ሳልህ የስልጣን ዘመን አብቅቷል። ከቁስሉ አገግሞ ወደ የመን ቢመለስ እንኳን የምትጠብቀው እሱ የማያውቃት የመን ናት።

ለመሆኑ እኛ ከየመን ምን እንማራለን?

- ድህነታችን፣ ኋላቀርነታችን፣ የበርካታ ዘውጌ ማኅበረሰቦች ውጤት መሆናችን ህዝባዊ አብዮቱን ያከብዱት እንደሆነ እንጂ  እንዳይነሳ እንደማያደርጉት ከየመን መማር እንችላለን።
- በጽናት የታገለ ህዝብ ድልን ሳይቀዳጅ ቤቱ እንደማይመለስ ከየመን እንማራለን።
- በህዝብ መጠላታቸው ፊት ለፊት ሲነገራቸው ለማይገባቸው ለእንደ አሊ አብደላ ሳልህ ዓይነቱ አምባገነኖች ከሰላማዊው ትግል ጎን የጡንቻ አስፈላጊ የቱን ያህል ወሳኝ እንደሆነ ከየመን እንማራለን።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የየመን የነፃነት ታጋዮች ላደረጉት ተጋድሎ ያለውን አድናቆት እየገለጸ ለተቀዳጁት ድል የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት ያስተላልፋል። ኮርተንባችኋል። በቅርቡ የተሟላ ድል እንደምትቀዳጁ ባለሙሉ ተስፋ ነን።

እኛም በቅርቡ የናንተን መንገድ እንከተላለን። አምባነንነት፣ ረሃብና እርዛት፣ ግፍ እኛም እንደናንተው መሮናል፤ አንገፍግፎናል። እንደናንተው እኛም "በቃ!" ብለናል።

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!!  አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

### መነሻ ዋጋው አምስት መቶ ብር የነበረው የአባይ ቦንድ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ወጥቶ ህዝብ ገንዘቡን ላለመስጠት ፊቱን ከማዞሩም በላይ "አባይ ከመገደቡ በፊት የዋጋ ንረቱ ይገደብ" በማለት ጥያቄ ማቅረብ ጀምሮአል ብሎአል።  ህዝብ ለወያኔ የአባይ ግድብ ግንባታ ፕሮፖጋንዳ የሰጠውን ጆሮ ያዳፈነውና ለአጭር ጊዜ ታይቶ የነበረውን መነሳሳት ያዳከመው በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን የሚሰጡት  አስተያየቶች እንደሆነ የህዝብ አስተያየት ያመለክታል።

በህዝቡ የቦንድ መግዛት ፍላጎት መቀነስ የተበሳጨው ዘረኛውና ሰው በላው የወያኔ አገዛዝ፣ በአባይ ግንባታ ላይ አሉታዊ አስተያየት የሚሰጡ ወገኖችን ሊታገሳቸው እንደማይችል ቢያስጠነቅቅም፣ ህብረተሰቡ ለወያኔ ዛቻና ማስፈራሪያ  ጆሮ አለመስጠቱ ታውቁአል።

ኢሳት ከዚሁ ዜና ጋር በማያያዝ ባወጣው ዘገባው ከ20 ሚሊዮን ብር ባላነሰ ወጪ የተሰራው የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ፎቶ ግራፍ የያዘ ቢልቦርድ በየክልሉ ከተሞች መሰቀል መጀመሩን ገልጾ ምንም እንኳ የመለስ ጋሻ ጃግሬዎች የጌታቸውን ስብዕና ለመገንባት እንዲህ አይነት እርምጃ ቢወስዱም ግለሰቡ በሰራቸው ወንጀሎች በህብረተሰቡ ዘንድ እየተጠላ ሂዶአል ብሉአል።

### ከፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ጋር ውይይት ያካሄዱት ኢትዮጵያዊያን . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ዘጋቢያችን አንዳንድ በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦችን ተዘዋውሮ በማነጋገር ባሰባሰበው መረጃ ኢትዮጵያዊያን አርቲስቶች ኢትዮጵያ ውስጥ የኢትዮጵያ መንግስት በዜጎች ላይ እየፈጸመ ያለውን ግፍና በደል አይተው እንዳላዩ ሰምተው እንዳልሰሙ በመሆን፣ ስለቅጂ መብት ብቻ አውርተው መውጣታቸው በጣም የሚያሳዝን ጉዳይ ነው፣ ከዚህም አልፈው ተርፈው እንደመለስ ላለ ዘረኛና ገዳይ ግለሰብ የወርቅ ብእር በስጦታ ማቅረባቸው    በጣም የሚያሳፍርና እነኝህ አርቲስቶችም ምን ያህል ስብእናቸው የወረደና ለህሊናቸውም ያላደሩ መሆኑን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

አያይዘውም እነጥላሁን ገሰሰን አይነት ታላላቅ አርቲስቶች የነበሩዋት ኢትዮጵያ ዛሬ በእንዲህ አይነት ህሊናቸውን በሸጡና ለሆዳቸው ባደሩ አርቲስቶች መጥለቅለቁዋ እጂግ የሚያሳዝን ነው ካሉ በሁዋላ  አርቲስት ማለት በተለያየ መድረክ ህብረተሰቡ ውስጥ ዘልቆ  የሚገባና የህብረተሰቡን እውነተኛ የኑሮ ሁኔታ የሚያንጻባርቅ ሆኖ እያለ የኛዎቹ አርቲስቶች ግን እያደረጉ ያለው ተግባር አሳፋሪ ብቻ ሆኖ የሚቀር ሳይሆን በታሪክ ተጠያቂ ሊያደርጋቸው   እንደሚችል ልብ ሊሉት ይገባል በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

### ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የግንቦት ሃያ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንደ ሪፖርተር ዘገባ የኦዲተር መስሪያ ቤቱ ባወጣው ማስታወቂያ ‹‹የመሥሪያ ቤቱን ጥሪ ተቀብለው በግንቦት 20ው የህዳሴ ግድብ ግንባታ ላይ ለተገኙት ምስጋና የቀረበ ሲሆን ያልተገኙት በሦስት ቀን ውስጥ ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ የታዘዙበት ምክንያት ጉዳዩ ከሥራ ዲሲፕሊን ጋር የሚገናኝ ነው መባሉን የመስሪያ ቤቱን የሥራ ሃላፊ ዋቢ በማድረግ  ተገልጾአል።

የሪፖርተርን ዘገባ አስመልክቶ ዘጋቢያችን አስተያየት እንዲሰጡት ያነጋገራቸው ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ የኦዲተር መ|ቤቱ ሰራተኞች በሰጡት አስተያየት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ  ኢትዮጵያዊያን በራሳቸው ፍቃድ ድጋፍ ለመስጠት ወጡ በማለት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥናና ሬዲዮ ጆሮአችንን የሚያደነቁረው ምን ያህል ውሸት እንደሆነ ከዚህ በላይ ገላጭ መረጃ የለም።  እንዲህ አይነት አሳፋሪ ተግባር አሁንም ከሃያ ዓመታት በሁዋላ እንደገና መከሰቱ እጂግ  አሳዛኝና አሳፋሪ ነው ብለዋል። በመቀጠልም የወያኔ ሃይል አካልን ሊያስር ይችላል፡ አስተሳሰብን ግን ሊያስር አይችልም። የአካል መታሰር በራሱ አስተሳሰብን እንደማይገድል ወያኔ ከደርግ ሊማር በተገባው ነበር ካሉ በሁአላ  የወያኔው ኦዲተር መስሪያ ቤት ባለስልጣን  ስለወያኔ ኢህአዴግ አንድ መልዕክት እያስተላለፈች ነው፤ ይሄውም ለግንቦት 20 እና ለግድቡ ሰልፍ ህዝብን ያስወጡት በየመስሪያ ቤታቸው እያስገደዱና እያስፈራሩ ነው ማለት ነው።    በማለት አስተያየታቸውን ማጠቃለላቸው ታውቁአል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ለግንቦት ሃያ ቀን በአል አከባበር የመንግስት ሰራተኞችን፣ ተማሪዎችን፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ተቀጠሪ ሆነው የሚሰሩ ዜጎችን ሁሉ በአሉ ሰልፍ በግድ እንዲወጡ ዛቻ የተሞላበት ትእዛዝ ያስተላለፈ ቢሆንም የታቀደውን ያህል ተሰላፊ በወቅቱ እንደአልወጣ መዘገባችን ይታወሳል።

# የህዝባዊ እምቢተኛነት የነጻነት ትግል በፖለቲካ ድርጅቶች የመመካከርና የመተባበር አጀንዳ ላይ ያሳደረው ተጽእኖ

(ለግንቦት 7 አባላት ለውይይት የቀረበ ጽሁፍ፤ ግንቦት 2003) (ክፍል 2 )

### 3. ማነው አደገኛ - ህዝብ ወይስ የፖለቲካ ድርጅቶች?

የፖለቲካ ድርጅቶች በመካከላቸው ያሉትን እውን ወይም እውን ያልሆኑ ልዩነቶቻቸውን አስወግደው መሰባሰብና መጠናከር እስከሚችሉ ድረስ ወጣቱ እጁን አጣጥፎ ይጠብቅ ከተባለ ለዘላለሙ በባርነትና በድህነት እንዲኖር እንደመፍረድ የማይቆጠረበት ምንም ምክንያት አይኖርም።

ሰሞኑን የወያኔ ተቃዋሚ ነን ከሚሉ ግለሰቦችና ቡድኖች "ጥንቃቄ እናድርግ" በሚል ምክንያት የሚቀረቡ ጽሁፎች በአለማችን በተለይ በአፍሪካና በመካከለኛው ምስራቅ ዉስጥ በፍጥነት እየተቀየረ ያለውን ሁኔታ ያገናዘቡ አይመስሉም። "የኢትዮጵያ ህዝብ በወያኔ ላይ ቢያምጽ አገሪቱ ታላቅ ቀውስ ላይ ትወድቃለች። የሃገሪቱ ጠላቶች የሆኑ የውጭ ሃይሎች አጀንዳቸውን ለማስፈጸም ቀውሱን ሊጠቀሙበት ይችላሉ። የመገንጠል አላማ ይዘው የተቀመጡ ሃይሎች የወያኔ መንግስት በህዝባዊ እምቢተኛነት ቢናጋ የመገንጠል አላማቸውን ለማሳከት እድል ያገኛሉ" እያሉ ነው። መፍትሄ ብለው የሚያቀረቡት ሃሳብ የድርጅቶች ትብብርና ህብረት በቅድሚያ እንዲኖር ማድረግ እንጂ ይህን ወጣት ለመደገፍ ምክክር አያስፈልግም የሚል ነው። ህዝቡ በተለያዩ ሃገሮች ያለፖለቲካ ድርጅቶች መሪነት በራሱ እንዲያምጽ ያደረገው ይህን ትብብር ተቃዋሚ ድርጅቶች ለአመታት ማምጣት የተሳናቸውና ፖለቲካዊ ሃላፊነታቸውን መወጣት አለማቻለቸው እንደሆነ እነዚህ ሃይሎች የተረዱት አይመስልም። ለመሆኑ በሁሉ ጉዳዮች ላይ ያለቀለት ካልሆነ በስተቀር በመለስተኛ የጋራ አላማዎች ዙሪያ መተባበር አይቻልም ወይ? ለመሆኑ "እኛ ዝግጁ አይደለንምና የህዝባዊ እምቢተኛነቱ ቁጣ ቢቀሰቀስ በሃገሪቱ ውስጥ ቀውስ ይፈጠራል። መጀመሪያ እኛ ዝግጁ እስክንሆን የመለስን መንግስት አትነካኩት" የሚል መልእክት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ለማስተላለፍ ምን የሞራልና የስራ ሬኮርድ አለን? የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ቱኒዝያና ግብጽ ህዝብ ተነስቶ "መብቴ ይከበር" ቢል ከዚህ የመብት የማስከበር ፍላጎት ውጭ ተንቀሳቅሶ አገር የሚጎዳበትሁኔታ ሊኖር ይችላል የሚል ስጋት ሊኖረን ይገባል ወይ? በጋራ የግፍና የሰቆቃ የድህነትና የውርደት ህይወት ተሳስሮ፣ ከዳር እስከ ዳር ባንድነት በመለስ ዜናዊ ላይ የሚነሳው ህዝብ ነው ወይንስ የራሳቸው ጠባብ የድርጅት አጀንዳዎችና የስልጣን ፍላጎቶች ያሏቸው ድርጅቶች ናቸው ለኢትዮጵያ ህዝብ የሰላም፣ የዴሞክራሲና አንድነት አደጋ የሚሆኑት? ያለፉት 20 አመታት ከተፈለገም ከዛ በላይ የሚዘከርለት የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የነጻ አውጭነት ታሪክ ምን ያህል አስተማማኝ ነው? "የተደራጀ አምባገነን በአንድነት ተባብረን እንደ አንድ ሰው ሆነን ካልገጠምነው ለዘላለም ባሪያ አድርጎ ሊገዛን ነውና በአንድነት እንነሳ" በሚል የጋራ ግንዛቤ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጀርባ መነጋገር የጀመረ ህዝብ መለስን በማስወገድ ወይም በማንገዳገድ የአንድነትን ሃያልነት በሚረዳበት ወቅት እንዴት ሆኖ አንድነቱን የሚያናጉና የሌላ አምባገነንና ዘራፊ ቡድን ሲሳይ ሊያደረጉት ወደሚችሉ ራስን የማውደም ተግባር የሚመለሰው? የቅርብ ጊዜ አብዮቶች ይህን አይነት የህዝብ አላዋቂነት የጠቆሙበት ማስረጃ አለ ወይ? በደንብ ከተመለከትነው ማስረጃው ከዚህ የተለየ ነው። በየሃገሩ የተገረሰሱ አምባገነኖች በየሃገሩ እንደነበሩ ደካማ ተቃዋሚዎች ቢሆን ኖሮ በድርድርና በስምምነት በስልጣናቸው ላይ በቀጠሉ ነበር። ለፈጸሙትም ወንጀል ተጠያቂ ባልሆኑ ነበር። ህዝብ ባንድነትና በጽናት ቆሞ "ድርድር የለም፤ መንፏቀቅ የለም። በቃ!" ባይላቸው እንሙባረክ ለልጆቻቸው ስልጣናቸውን ለማውረስ ተቃዋሚው የሚጋርጥባቸውን ፈተና ለማለፍ የሚያስቸግራቸው አይሆንም ነበር።

በሃገራችን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ምን አይነት ድርጅቶች እንደሆኑ፤ በምን ያህል ትጋትና እልህ እንዲሁም የሁኔታዎችን አሳሳቢነት ግምት ውስጥ እያስገቡ በጥድፊያ እንደሚሰሩ፤ ምን ያህል አባላትና ድርጅታዊ መዋቅር እንዳላቸው፣ በማስፈራሪያና በድለላ የያዙትን አቋም በቀላሉ ሊቀይሩ እንደሚችሉ ብዙ ከህዝብ የተሰወረ ጉዳይ አይደለም። ህዝብ ያለው ትልቅ ተስፋ የራሱን የነጻነት ትግል ራሱን አታጋይና ታጋይ አድርጎ የሚከፈለውን መስዋእትነት ከፍሎ ማረጋገጥ ብቻ ነው። የቱኒዝያና የግብጽ ህዝብ ለማድረግ የሞከረው ይህንኑ ነው። ግብጾችን ቱኒዝያኖች ከኢትዮጵያውያን የተለዩ ፍጥረቶች ናቸው ካላልን በስተቀር የሃገራችን ወጣቶች "ለነጻነታችን ልንነሳ ነው" ሲሉ "ተው ጠብቁን" የምንልበት ምክንያት ሊኖር አይችልም፤ አይገባምም። እንዲያውም ያለንበትን ሁኔታ በደንብ ከተመለከትነው ጠንካራ ድርጅቶች ወይም ድርጅት በሌለበት ሁኔታ የአንድ ሃገር ህዝብ በስፋት ተነስቶ የራሱን የወደፊት እጣ በጁ ማስገባት የሚችለበት እድል መገኘት አምባገነንትን ከአንድ ሃገር ላይ ለአንዴና ለመጨረሻው መቅበሪያ ፍቱን መሳሪያ ነው። በጠንካራ ድርጅቶች ከሚመራ የዴሞክራሲ የለውጥ እንቅስቃሴ ይልቅ ለራሳቸው ህይወት ሃላፊነት በወሰዱ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎችና በሽዎች የሚቆጠሩ የዜጎች ቡድኖች የሚመራ ትግል ለዴሞክራሲ ግንባታ ተመራጭና አስተማማኝ ነው። የህዝብ አቅም ሳይደረጅ የድርጅቶች አቅም ከሚገባው በላይ ማደግ ለህዝብ አደጋ ያረገዘ አካሄድ ነው። ህዝብ በሚነሳበት ወቅት መስዋእትነቱ መና እንዳይቀር መደረግ ያለበትን ዝግጅትና ጥንቃቄ እንዲደረግ የራሳችን ሃላፊነት እስከተወጣን ድረስና የህዝብም ትግል በድል እስከተጠናቀቀ ድረስ የድርጅቶች ትብብር ጠንካራ ሆነ አልሆነ ከዲሞክራሲ ግንባታ አንጻር ካየነው የሚሳሳብ ጉዳይ አይደለም።

ድርጅቶችና መሪዎች የዴሞክራሲና የነጻነት ቃል ኪዳናቸው ሊሰብሩ የህዝብ አደራ ሊበሉ ይችላሉ። ህዝብ ግን ራሱን በራሱ የሚጎዳ ስራ ስለማይሰራ ለገዛ ነጻነቱና መብቱ ዘላለም ዘብ ይቆማል። በኢትዮጵያም የሃገሪቱ ተቃዋሚ ድርጅቶች ደካማ በሆኑበት ሁኔታ ህዝብ የተሳካ የህዝባዊ እምቢተኛነት ቁጣ ማቀጣጠል ከቻለ ለህዝብና ለሃገር የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ አይደለም። የህዝብ ጉልበት ከድርጅቶች ጉልበት በላይ የሚያይለበት ሁኔታ በሃገራችን ቢከሰት በየጊዜው ስልጣን ለሚይዙ አምባገነን ባለጌዎች መቀለጃ ሆኖ ስቃዩ ማብቂያ ላጣው የሃገራችን ህዝብ እንደጸጋ መታየት ይኖርበታል። ስለዚህ ህዝብ "ለመብቴ እነሳለሁ!" ሲል መልሳችን "እንዴት በጥድፊያ እናግዘው?" ነው እንጂ ይህን እገዛ የሚያጓትቱና በአንድነት መቆም የሚገባቸውን ድርጅቶችንና ቡድኖችን በማይረባ እንቶ ፈንቶ የሚጠመዱ አጀንዳዎችን መክፈት፣ ማስፈራሪያዎችን ማሰራጨት የወቅቱ ተገቢ ምላሽ አይሆንም።

### 4. አዲሱ ዘመን - አዲስ አይነት ትብብር

ባሁን ወቅት የሚስተጋባው የትብብር ጥሪ "ግንባር እናቁም፤ ትብብር እንፍጠር፤ መድረክ እናዘጋጅ፤ ወያኔን ለመተካት የሚችል የቀውጢ ጊዜ ግብረ ሃይል ወይም ተተኪ መሆን የሚችል የመንግስት ቅጂ (ጥላ) እናቁም" አይደለም። "የተለያዩ የድርጅት ፕሮግራሞችና ፖሊሲዎቻችን እናቀራርብ" የሚልም አይደለም። ደግመን ደጋግመን እንለዋለን ድርጅቶች ጠንካራ ህብረቶችን ፈጥረው መገኘታቸው አስፈላጊም ጠቃሚም ነው። ቀደም ብለን እንደጠቀስነው የተቃዋሚዎች አቅም በአንድ ተደምሮም ዝቅተኛ በመሆኑ ህዝብን የሚያስፈራ አይሆንም። ከአቅማቸው ማነስ የተነሳ ተቃዋሚዎች ባንድ ላይ ተሰብስበውም ባሁኑ ወቅት ህዝብን ከማበረታት አልፈው የመሪነት ሚና መጫወት አይችሉም። ለትብብር መፍጠር የሚደረገው ሙከራ አሁንም ይቀጥል። ነገር ግን አዲሱ ዘመን ይዞት የመጣውን አዲስ የትብብር እይታም በደንብ እንፈትሸው።

የግብጽና የቱኒዝያ አብዮቶች ያስተማሩን ትምህርት ህዝብ የሚቆጣጠረው የለውጥ ሂደት በፖለቲካ ፓርቲዎች መሃከል ያለውን ማናቸውንም ልዩነት ወደ ዝቅተኛ ደረጃ ማውረድ እንደሚችል ነው። ቅድሚያ ሁሉንም የሃገሪቱ ዜጎችና የፖለቲካ ድርጅቶች በእኩልነት የሚያስተናግድ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ ለመፍጠር ለሚደረገው ትግል መስጠት እንደሚቻል ነው። የቱኒዝያና የግብጽ ህዝባዊ እምቢተኛነት የፖለቲካ ድርጅቶችን የለውጥ መሪነት ወይም ተቆጣጣሪነት ሚና በመዝጋትና በብዙሃን ቡድኖች አማካይነት በህዝብ ለሚከወን አብዮት እድል በመክፈት የትግሉን ህዝባዊ አንድነትንና የተነሳበትን አላማ መከላከል ችሏል።

ከህዝብ ጀረባ በልሂቁ መሃከል በሚደረግ የሰጥቶ መቀበል ድርድር ስልጣን ለመያዝ የሚደረግ ትብብር የዘመኑ የትብብር ጥያቄ አይደለም። ህዝብም እንዲህ አይነቱን አግላይ የፖለቲካ አካሄደ እሺ ብሎ የሚቀበልበት ዘመን አልፏል። ያለንበት ዘመን የፖለቲካ ድርጅቶች መተባበር ጽንጸ- ሃሳብ ቀላልና ኩልል ብሎ የሚታይ ነው። ተሰባስበን ተመካክረን ተባብረን ህዝብ በራሱ መሪነት ሊያከናውነው የሚፈልገውን የነጻነት ትግል እንዴት እንደግፍ በሚል ጉዳይ ላይ ያተኮረ ነው፤ የዘመኑ የትብብር ጥሪ። የተወሳሰበ ድርጅታዊ መዋቅር፣ ሰነድ፣ የግንባር የስልጣን ክፍፍል ወዘተ የመሳሰሉ አጨቃጨቂ ጉዳዮች የሉትም ። መሃመድ ቦዓዚዝ ራሱን አቃጥሎ የቱኒዝያ ህዝብ በቁጣ እንዲገነፍል ካደረገበት እለት ጀምሮ ግንቦት 7 ከየትኛውም ድርጅትና ቡድን ጋር ያደረገው የትብብርና የምክክር ስራ የዘመናችን የለውጥ እንቅሰቃሴ ግምት ውስጥ ያስገባ ነው።

ህዝብ በግብጽ እንደታየው በአንድነት ለነጻነቱና ለዴሞክራሲያዊ ስርአት መመስረት እንዲነሳ ራሱን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች ተሽመድምደን የምንገኘን የፖለቲካ ድርጅቶችን ነጻ እንዲያወጣ ምን ማበርከት እንችላለን? ህዝብ ማንም ሳይጠበቅ የሚነሳ ከሆነ ጥረቱ እንዲሳካ ለህዝብ ምን ድጋፍ ልናደረግ እንችላለን? ይህ ነው ያለፉት ጥቂት ወራት የግንቦት7 ንቅናቄን ትኩረት የሳበው። ባለፉት ጥቂት ወራት ግንቦት7 ግንባር፣ ቅንጅት ወይም ውህደት እንፍጠር በማለት ያነጋገረው ድርጅት የለም። የፈጠረውም ግንባር የለም። ትልቁንና ብዙ ጣጣዎች ያሉትንና ብዙዎች ብዙ ጊዜ ሞክረውት ያልተሳካ ከባድ የግንባር፣ የቅንጅትና የውህደት መፍጠር ስራ ግዜውን ጠብቆ በሂደት ሊከናወን እንደሚችል እምነት አለን። ይህ ሂደት አዝጋሚ ነውና ፈተናዎቹ ብዙ ናቸውና እንተወው አላልንም። ሆኖም ግን ባለፉት ጥቂት ወራት ንቅናቄያችን ያተኮረው እጅግ አጣዳፊ በሆኑና በቀላሉ በመመካከር ሊፈጸሙ በሚችሉ የጋራ ጉዳዮች ላይ ነው። ለነጻነቱ የሚነሳውን ህዝብ በጋራ የመታደግ ስራ ላይ ነው። "ለህዝብ መብት መከበር ቆሚያለሁ" ከሚል ማናቸውም ሃይል የሃገራችን ወጣትና ህዝብ በአሁኑ ወቅት የሚጠብቀው ይህን ብቻ እንደሆነ እርግጠኞች ነን።

ሁላችንም በፖለቲካው መድረክ የምንቀሳቀስ ድርጅቶች ቡድኖችና ግለሰቦች ልብ ልንለው የሚገባ ሌላ ሃቅ አለ። ዛሬ ሁላችንም የኔ እያልን የምንጠራቸው፤ በየትኛውም ኪሳራ ህልውናቸውን ልንከባከብላቸው የምንጥራቸው ድርጅቶቻችን ወደፊት በሃገራችን ውስጥ በሚቀሰቀሰው ሰፊ ህዝባዊ የነጻነት ማእበል ወስጥ እጣቸው ምን እንሚሆን ለመተንበይ አስቸጋሪ መሆኑን ነው። ስለትብብር፣ ስለ ሽግግር መንግስታዊ ስርአት መመስረት ስናወራ ሁኔታዎች እንዳሉ ይቀጥላሉ የሚል እሳቤ እያስቀመጥን ነው። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ለመብታቸው በሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ታፍኖ ከኖረው ህዝብ መሃል አዲስና ግዙፍ ድርጅቶች ሊወለዱ፣ የህዝብን አመኔታ የሚያገኙ ታላላቅ መሪዎች ብቅ ሊሉ ይችላሉ። ዛሬ ያለነውን ድርጅቶች ላይ በማተኮር "የሃገሪቱ ፖለቲካ አልፋና ኦሜጋ እኛ ብቻ ነን" የሚል መንፈስ ሁሉን አድቀን ወስነን ጨርሰን እንሂድ የሚል የትብብር አመለካከት ይህንንም እውነታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል።

ከህዝባዊ እምቢተኛነት የፈለቀው አዲሱ የትብብር ቀመር ለድርጅቶች ብትህውትነት ያስተማረ ይመስለናል። "ያለኔ የህዝብ ተጠሪ የለም። ያለኔ ዲሞክራሲ አይኖርም።ያለኔ ሃገር ይፈረሳል። ህዝብ እርስ በርሱ ይጫረሳል" የሚለውን የየሃገሩን ልሂቅ ትምክህት አስተንፍሷል።

(ክፍል 3 ሳምንት ይቀጥላል)

### በኦጋዴን አካባቢ ያለው ውጥረት ከዘረኛው አገዛዝ ቁጥጥር ውጪ እየሆነ መምጣቱ ታወቀ

በኦጋዴን አካባቢ ያለው የጸጥታ ሁኔታ ከመቼውም ጊዜ በላይ የተበላሸ ደረጃ ላይ መድረሱንና ባለፈው ሳምንት ብቻ ሰባት የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ወታደሮች በኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት ታጣቂዎች ተገድለው ጅጅጋ ከተማ ውስጥ መቀበራቸውን የአይን እማኞችን ዋቢ በማድረግ ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት እውነታው ይህ ሆኖ እያለ ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በቁጥጥሩ ስር ባሉት የዜና አውታሮች አማካኝነት በአካባቢው ምንም አይነት ችግር እንደሌለ በመግለጽና ሰላምም እንደሰፈነ በማስመሰል የሚያቀርበው ዘገባ ፍጹም ከእውነት የራቀ እንደሆነ የአካባቢው ነዋሪዎች መናገራቸውን አያይዞ ገልጿል።

ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አንዳንድ የአካባቢው ተወላጆች እንደተናገሩት የዘረኛው አገዛዝ ወታደሮች የኦጋዴን ነዋሪዎችን ተሽከርካሪዎች በጠመንጃ ሃይል በመቀማትና መኪኖቻቸውንም ያለክፍያ ለወራት ወደ በረሀ በመውሰድ መጠቀም መጀመራቸውን ገልጹአል። በመቀጠልም ወታደሮቹ በኦጋዴን በነዋሪዎች ላይ የሚፈጽሙት ግድያ እስራትና ዝርፊያ ነዋሪዎቹ በየጊዜው ተቃዋሚዎችን እንዲቀላቀሉ መንገድ እየከፈተላቸው እንደሆነ ተገልጹአል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባለፈው ዓመት ከኦጋዴን ነጻ አውጭ ድርጅት አንድ ክንፍ ጋር የሰላም ስምምነት ማድረጉን ቢያስታውቅም፣ ተደረገ የተባለው ስምምነት በአካባቢው በሚኖሩ ሌላ ብሄረሰብ አባላት ላይ ወይም በአካባቢው አጣራር ደገኞች በሚባሉት ላይ ስቃይ ከመጨመር ያለፈ የፈየደው ነገር እንደሌለ ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቶአል።

የኢህአዴግ አጋር ድርጅትና የክልሉ ገዢ ፓርቲ የሆነው ሶህዴፓ አባላት በደገኞች ላይ የሚፈጽሙት ግፍ ወደር እንደሌለው ዘጋቢያችን አካባቢውን ነዋሪዎች በማናገር ዘግቧል።

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ በኦጋዴን ክልል የትጥቅ ትግል የሚያካሂደው የኦጋዴን ብሄራዊ ነጻነት ግንባር ባደረገው ከፍተኛ የጥቃት እርምጃ ጅጅጋ አካባቢ የሚገኘውን የጋላሽ ከተማን ተቆጣጥሮ በመቶዎች የሚቆጠሩ እስረኞችን ነጻ ማውጣቱንና ብዛት ያላቸው የጦር መሳሪያዎችን መማረኩን መግለጹ በስፋት መዘገቡ ይታወሳል። እንደ ኦብነግ መግለጫ ከእስረኞቹ መሀል ከሶስት ሳምንት በላይ የደረሱበት ሳይታወቅ የቆዩት ሁለት የተባበሩት መንግስታት የአለም ምግብ ድርጅት ሰራተኞች የሚገኙበት ሲሆን ባለፈው ሜይ 23 ቀን በአለም የምግብ ድርጅት ሰራተኞች ላይ በደረሰው ጥቃት ሹፌሩ ሲገደል ሁለት ሰራተኞች ደግሞ የደረሱበት ሳይታወቅ መቆየቱ ይታወሳል:: የግድያውንም ሆነ የአፈናውን እርምጃ ያካሄዱት የወያኔው ኢህአዴግ ታጣቂዎች ናቸው ሲሉ የኦብነግ ቃል አቀባይ ይፋ ማድረጋቸው አይዘነጋም።

### የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አሁንም ትምህርት አልጀመሩም፣ ዩኒቨርስቲው አሁንም በፌደራል ፖሊስ ቁጥጥር ስር ነው

ካለፈው ግንቦት 22 ጀምሮ ዩኒቨርሲቲው ያቀረብነውን የመብት ጥያቄ በአግባቡ ይመልስልን ያሉ የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ይህ ሪፖርት እስከተጠናከረበት ድርስ ትምህርት አለመጀመራቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

ተማሪዎቹ ያነሱት የመብት ጥያቄ ወደ ሌሎች ቦታዎች እንዳይዛመት ፍርሃት የገባው የወያኔ አገዛዝ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የፌደራል ፖሊስ እንዲሰፍር ካደረገ በኋላ ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ ትዕዛዝ ያስተላለፈ ቢሆንም ለሞቱትና ለቆሰሉት ተማሪዎች ተጠያቂ የሆኑት ለፍርድ ካልቀረቡ ትምህርት ለመጀመር ፍቃደኛ እንዳልሆኑ መግለጻቸውን የዩኒቨርሲቲው ምንጮቻችን ለዝግጅት ክፍላችን ከላኩት መረጃ ለማረጋገጥ ተችሎአል።

ከትናንትና በስቲያ ሃሙስ ወደዩኒቨርስቲው ተልኮ የነበረው የወያኔ የክልሉ ሹመኞች ቡድን በተነሳው ረብሻ ምክንያት 40 ሚሊዮን ብር በላይ የሚገመት የዩኒቨርስቲው ንብረት እንደወደመ አስረድቶ ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን በአስቸኳይ እንዲጀምሩ አለዚያ የከፋ እርምጃ እንደሚጠብቃቸው ለማስፈራራት ቢሞክርም፤ መብታቸውን ለማስከበር ቆርጠው የተነሱት የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲው የሰፈረው ፌደራል ፖሊስ ግቢውን ለቆ ካልወጣ ለህይወታቸው ዋስትና እንደሌላቸው በመግልጽ ገዳዮች ለፍርድ እንዲቀርቡ ካቀረቡት ጥያቄ ፈቀቅ እንደማይሉ ወኔ በተሞላበት ድፍረት አስረድተዋል። በተማሪዎቹ አቋም የተደናገጠው የዩኒቨርስቲው አስተዳደር ይህ ሪፖርት አስከተጠናከረበት ሰዓት ድርስ ለተማሪዎቹ በቀን በነፍሰወከፍ ከሚሰጣው ሶስት ዳቦ በስተቀር መደበኛ ምግብም እንዳልጀመረላቸው ታውቆአል።

ለአባይ ግድብ ግንባታ ገንዘብ ከመለገስ ጋር በተያያዘ የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ በርካታ ተማሪዎች ቆስለው ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸው ታቅቋል።

### ህዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍን እነደጦር እየፈራ ያለው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ አርሶ አደሮች ተቃውሙአቸውን እንዳይገልጹ ከለከለ

በሰሜን ጎንደር ዞን በጭልጋ ወረዳ የሚገኙ አርሶአደሮች ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርጉ መከልከላቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት የዜና ወክኪሉን ዋቢ በማድረግ ዘገበ:: አርሶ አደሮቹ ተቃውሞአቸውን ለማሰማት ወደ ጎንደር ለመሄድ ዝግጅት በማድረግ እያሉ በታጣቂዎች መከልከላቸውን ተያይዞ የደረሰን ዜና አመልክቱአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ የጭልጋ ወረዳ አርሶአደሮች ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ አስበው የነበረው ባለፈው ቅዳሜ የግንቦት20 በአል በሚከበርበት እለት ሲሆን አርሶ አደሮቹ ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ የፈለጉት የወያኔ አባል ካልሆኑ በስተቀር ከባንኮች ምንም አይነት ብድር እንዳያገኙ የሚደረገው አሰራር አስመርሮአቸው እንደሆነና በአካባቢያቸው ያለውን የጣና ዙሪያ መሬት እንዳያርሱ በመከልከላችው ነው ተብሎአል።

የወያኔው ኢህአዴግ በቅርቡ የኢህአዴግ ደጋፊ ነጋዴዎች ፎረም ብሎ እንዳቋቋመው ሁሉ የኢህአዴግ ደጋፊ የአርሶአደሮች ፎረም ብሎ በማቋቋም ለደጋፊዎቹ የፎረም አባላት ከፍተኛ የሆነ ብድርና የእርሻ መሬት መስጠት በመጀመሩ ፤ የወያኔውን ኢህአዴግን አንቀሳቀልም ያሉ አርሶ አደሮችን እጅግ ማበሳጨቱ ታውቁአል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ FFSR (ኤፍ ኤስ ኤሴ አር) ተሽከርካሪ ከጭልጋ ከተማ ወጣ ብሎ በሚገኝ አንድ ወንዝ ላይ ታፍኖ በመወሰዱ በተሽከርካሪው ውስጥ ያሉ ሰዎች የደረሱበት አለመታወቁን የአካባቢው ነዋሪዎች መግለጻቸውን ኢሳት አያይዞ ዘግቡአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ አፈናውን ማን እንደፈጸመው የታወቀ ነገር አለመኖሩንና ከአካባቢው ነዋሪዎች ለመረዳት እንደሚቻለው የአካባቢው የጸጥታ ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ መምጣቱ ታውቋል።

### ጥራትና ደረጃውን ያልጠበቀ ዘይት ለህዝብ እየተሸጠ ነው፣ . . . 

(ከገጽ 1 የዞረ)

የዘረኛው ወያኔ አገዛዝ የተስማሚነት ምዘና ድርጂት ባለስልጣን እንዲህ አይነት አሰራር በህብረተሰቡ ጤና ላይ ሊያስከትል የሚችለው ችግር አይኖርም ወይ ተብሎ ተጠይቆ በሰጠው ምላሽ "ካለው ወቅታዊ ሁኔታ አንፃር የሚያስኬድ አግባብን በመከተል ነው ያሠራጨነው:: አዮዲን የሌለው ጨው እንዲሰራጭ ሕግ አይፈቅድም:: በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ወቅት ተፈጥሮ በነበረው እጥረት ምክንያት ግን የተገኘው አዮዲን የሌለው ጨው ነው፤" በማለት የተናገረ ሲሆን ከጤና ጋር በተየያያዘም "ለምሳሌ አንድ ግለሰብ የዘይት አለርጂክ ሊኖርበት ይችላል:: እናም በእንደዚህ ያለ አሠራር ችግር ያጋጥማል:: እጥረት ወይም ሌላ ተመሳሳይ ችግርን ለመፍታት በሚወሰድ ዕርምጃ እንደዚህ ያሉ አደጋዎች የሚጠበቁ ናቸው፤ ነገር ግን የጥንቃቄ ጉዳይ ግን ሁሌም ይኖራል፤" ማለቱ ታውቁአል::

ዘጋቢያችን በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑና ይህን ዘይት በመጠቀም ላይ ያሉ አንዳንድ ግለሰቦችን አነጋግሮ ባሰባሰበው አስተያየት ባሁኑ ሰአት እኛ ህይወታችንን ለአንዲት ቀንም ለማቆየት መመገብ አለብንና ምንነቱን ሳናውቅ ይሄው እየበላን እንገኛለን:: ባሁኑ ሰአት ኑሮአችን ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ነውና ዘይቱ ጊዜ አልፎበታል ወይም አላለፈበትም ሳንል ይሄው እየተጠቀምንበት ነው:: ተወደደም ተጠላ ወያኔ እዚች ሃገር ላይ በስልጣን እስካለ ድረስ ገና ብዙ ፍዳ እንደምንቆጥር ምንም የሚያጠራጥር አይደለም ብለዋል::

### ዘረኛውና አፋኙ የወያኔ አገዛዝ ኢትዮጵያዊያን . . . 

(ከገጽ 1 የዞረ)

በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ አባላቶቻችን እየታሰሩና እየተዋከቡ ነው “ ሲሉ መግለጻቸው ታውቋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ አዲስ ነገር በመባል የሚታወቀው የመረጃ ድረገጽ ባወጣው ዘገባው ያነጋገራቸው አንድ የምዕራብ ሸዋ ዞን የኦፌዴን አመራር አባል የወያኔው ኢህአዴግ ለእያንዳንዱ ዜጋ የሚኾን የሀሰት የክስ መነሻ አዘጋጅቶ እንደሚንቀሳቀስ መናገራቸውን ገልጹአል። አያይዞም “የወይኔው ኢህአዴግ አገዛዝ መብቱን የሚጠይቅ ኦሮሞን ለማጥቃት ሲፈልግ ኦነግ፣ መብቱን የሚጠይቅ አማራን ሲመጣ ደግሞ ግንቦት 7 እና ሌሎች ተለጣፊ ተቀጽላዎችን በመስጠት ዜጎችን በፍርሃት በመወጠር ተጠያቂነቱን እያጠፋ ነው” ፤ “ ለዚህም ቀደም ብሎ ያወጣውን የጸረ ሽብር ዓዋጅን እንዳሻው እየተጠቀመበት የዜጎችን ሰብዓዊ መብት ይገፍበታል” ብለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም ከምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ በአስር ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎችን በጅምላ አስሮ እነደነበረና ከዚያን ጊዜ ጀመሮ አስከዛሬ ድረስ በየቀኑ ቁጥራቸው በውል የማይታወቁ ዜጎችን የተለመደውን የፈጠራ ክስ እየመሰረተ አንደሚያስር ፤ እንደሚገል እና የደረሱበት እንዳይታወቅ እንደሚያደርግ በአለም ታዋቂ በሆኑ የሰብዓዊ መብት ተሚጋች ድርጅቶች ጭምር በተደጋጋሚ ክስ እየተመሰረተበት እንደሆነ ይታወቃል። መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ልያደርጉብኝ ሲሉ ደረስኩባቸው በማለት ከግንቦት 7 ንቅናቄ ጋር በማያያዝ ስም ክስ የመሰረተባቸው የጦር መኮንኖችና ሲቪሊያን ላይ በእስር ቤት ውስጥ፡ ለሂሊና የሚሰቀጥጥ አሰቃቂ ድብደባ እንደፈጸመ በሌሎች የኦነግ ተጠርጣሪ እስረኞች ላይም ተመሳሳይ ሰቆቃ እንደሚፈጽም ይፋ መደረጉ አይዘነጋም።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org